# የከፍተኛ ትምህርት፣ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ የምርምር ተቋማት እና የኢንዱስትሪ ትስስር

## የትብብር ስልጠና መመሪያ

## አጭር ማብራርያ (ሐተታ ዘምክንያት)

1. መግቢያ

የትብብር ስልጠና በከፍተኛ ትምህርት፣ በቴክኒክና ሙያ ሥልጠና፣ በምርምር ተቋማት እና በኢንዱስትሪ ዘርፍ መካከል ቅንጅታዊ አሰራር ስርአት ባለመኖሩ፣ ኢንዱስትሪው የሚፈልገውን ክህሎት የሚያሟላ ብቁ የሰው ኃይል ማፍራት እና የምሩቃን ስራ የማግኘት እድል ውስንነት ይስተዋላል። የትስሰር አካላትን በማሳተፍ የትብብር ስልጠናዎች ማከናወን ችግሩን ለመፍታት ቁልፍ ሚና አለው።

በኢንዱስትሪው የሚገኘውን መሰረተ-ልማት እና ሀብት በመጠቀም የትብብር ስልጠና መስጠት የከፍተኛ ትምህርት እና የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት ለመሰረተ-ልማት ግንባታ ሊያወጡ የሚችሉትን ተጨማሪ ወጪ ለመቀነስ እና ውጤታማ ስልጠና ለመስጠት ያስችላል።

በተጨማሪም የኢንዱስትሪውን ፍላጎት መሰረት ያደረገ የሰው ኃይል ማብቃት ስራ ላይ ኢንዱስትሪው ቀጥተኛ ተሳትፎ በማድረግ የሚሰጥ በመሆኑ ኢንዱስትሪው በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ የሚቀጥረውን ባለሙያ በአገር ውስጥ ለመተካት እንዲሁም በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው የሰው ኃይል በማፍራት የውስጥ አቅምን መገንባት ኢንዱስትሪዎችን ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ማድረግ የመንግሥት የልማት ትኩረት አቅጣጫ ነው።

2.አላማ

ይህ መመሪያ በትብብር ስልጠና አተገባበር አቅጣጫ የሚሰጥ ሲሆን የትብብር ስልጠናው የሚቀረጽበትንና የሚተገበርበትን ሂደት እንዲሁም የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በትግበራው ሂደት የሚሳተፉበትን የአሰራር ስርዓት እንዲኖር ለማድረግና የትስስር አዋጅ ቁጥር 1298/2015 ለማስፈጸም ነው፡፡

3. የባለድርሻ አካላት ድርሻ

የረቂቅ መመሪያው የዝግጅት ሂደት ላይ ከሁሉም የትስስር አካላት የባለሙያ ስብጥር ተዋቅሮ የተሰራ ሲሆን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት ማድረግ እና አስተያየት መቀበል ወሳኝ ምዕራፍ በመሆኑ ሁሉም የግልና የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች፣ የተመረጡ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማት፣ የተመረጡ ኢንዱስትሪዎች እና ምርምር ተቋማት እንዲሁም የተመረጡ የቴክኖሎጂና ሰው ሀብት ልማት ዘርፍ ተቋማት ተሳትፈውበት ግብአት ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ ባለድርሻ አካላት በተገኙበት በተለያየ መድረክ መመሪያው ቀርቦ ተተችቷል ግብአት እና የማስተካካያ ሀሳቦች ተወስደው ማስተካካያ ተደርጓል፡፡ የእያንዳንዱ ባለድርሻ አካል በትብብር

ስልጠና ላይ የተሰጡትን የማስተካከያ ሃሳቦች እና እያንዳንዱ እርማት ከዚህ ሰነድ በአባሪ ተያይዟል።

## 4. የመመሪያው ይዘት

መመሪያው በአስራ ስድስት አንቀጾች የተዋቀረ ነው። የዚህ መመሪያ የተፈጻሚነት ወሰን በከፍተኛ ትምህርት፣ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና፣ በምርምር ተቋማት እና በኢንዱስትሪ ትስስር አዋጅ 1298/2015 በተጠቀሱ የትስስር አካላት ላይ ነው።

የመመሪያው ክፍል ሁለት በአራት አንቀጾች የተዋቀረ ሲሆን የክፍሉ ዋና ሀሳብ የሚያጠነጥነው የትብብር ስልጠና ቀረፃ  እና አቀራረብ ላይ ነው። በሀገራችን የስርዓተ-ትምህርት ቀረጻ የኢንዱስትሪ ተሳትፎን የሚያረጋግጥ ባለመሆኑ የትብብር ስልጠና ስርዓተ-ትምህርት በሚቀረጽበት ወቅት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት እና ኢንዱስትሪዎች በትብብር እንዲያዘጋጁ እና ከኢንዱስትሪው እና ከትስስር አካላት ፍላጎት ጋር የሚጣጣም መሆን እንዳለበት ይደነግጋል።

የመመሪያው ክፍል ሶስት በሁለት አንቀጾች የተዋቀረ ሲሆን ስለ አሰልጣኞች እና የስልጠና ሰጪ አካላት ማሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች የሚደነግግ ነው። የትብብር ስልጠና ደረጃውንና ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን ስልጠናውን የሚተገብሩ አሰልጣኞች እና ተቋማት መሰረታዊ መስፈርት ማሟላትን ያረጋግጣል።

የመመሪያው ክፍል አራት በሶስት አንቀጽ የተዋቀረ ሲሆን ስለቁልፍ ተዋንያን ማለትም ኢንዱስትሪ፣ የስልጠና ሰጪ ተቋም እና ሰልጣኝ ተግባርና ኃላፊነት ይደነግጋል። ይህም የትብብር ስልጠና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የባለዘርፈ-ብዙ ባለድርሻ አካላት ቅንጅታዊ ተሳትፎን የሚፈልግ በመሆኑ ለባለድርሻ አካላት ግልጽ የሆነ ተግባርና ኃላፊነት ደንግጓል። የመመሪያው ክፍል አምስት በሶስት አንቀጽ የተዋቀረ ሲሆን ስለ መመሪያውን የማስፈጸም ኃላፊነት፣ መመሪያውን ስለማሻሻል፣ መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ፣ የትስስር አካላት ይህንን መመሪያ ለማስፈጸም እንደተቋማቸው ነባራዊ ሁኔታ የውስጥ መመሪያ እንዲያወጡ ሙብት እና ኃላፊነት ይሰጣል።

## 5. ህጉን ለማርቀቅ መነሻ የሆነ ፖሊሲ እና አዋጅ ስለመኖሩ፤

ረቂቅ መመሪያው ከአገሪቱ ህጎች ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ከትስስር አዋጅ ቁጥር 1298/2015፣ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ እና  የሳይንስ፣ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ፖሊሲ ጋር መናበብ እንዲኖር

እና ሌሎች ተዛማጅ የህግ ማእቀፎች ቅኝት ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የትስስር ስራ ተግዳሮት ለመለየት የተደረገ የዳሰሳ ጥናት እንደመነሻ ተወስዷል።